በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

ሰኔ 16 ቀን 2012
አዲስ አበባ

# 88ኛ መደበኛ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ስብሰባ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 88ኛ መደበኛ ስብሰባ በተለያዩ አጀንዳዎች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

1. ምክር ቤቱ በቅድሚያ የተወያየው በመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ ፖሊሲ ላይ ሲሆን የብሮድካስት ባለስልጣን የመገናኛ ብዙሃን ዘርፍ የሚመራበት ራሱን የቻለ የመገናኛ ብዙሃን ፖሊሲ ባለመኖሩ ዘርፉን በብቃትና በጥራት ማስፋፋትና ሁሉንም ዜጎች የመረጃ ተደራሽ ማድረግ አለመቻሉን በመግለጽ የአገራችን የመገናኛ ብዙሃን የሚመራበትና የሚደገፍበት፣ ሃገራችን ከምትከተለው የፖለቲካ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ፣ ከመሰረታዊ የሰው ልጅ የሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብትና ህግጋት፣ ከህብረተሰቡ ባህል፣ እሴት፣ አመለካከትና ፍላጎት እንደዚሁም በዘርፉ ካጋጠሙ መሰረታዊ ተግዳሮቶች፣ ከቴክኖሎጂ ውጤቶችና መሰል ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የተጣጣመ የፖሊሲ ሰነድ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ የመገናኛ ብዙሃን ረቂቅ ፖሊሲ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡ ምክር ቤቱም በቀረበው ረቂቅ ፖሊሲ ላይ በዝርዝር ከተወያየ በኋላ የተሰጡ ግብዓቶች ተካተው በስራ ላይ እንዲውል ወስኗል፡፡

2. በመቀጠልም ምክር ቤቱ የተወያየው የኤክሳይስ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012 ለማሻሻል በቀረበው ረቂቅ አዋጅ ላይ ነው፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 43(1) ተሻሽሎ ከዚህ በታች በተመለከተው አዲስ አንቀጽ 43(1) እንዲተካ የማሻሻያ ሃሳብ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲቀርብ ወስኗል፡፡

> "አንቀጽ 43(1) በዚህ አዋጅ ምዕራፍ 3 ክፍል 1 ፈቃድ ስለማውጣት የተደነገገው ቢኖርም የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች በማምረት ወይም አገልግሎት በመስጠት የተሠማራ ማናቸውም ሰው ፈቃድ ባይኖረውም ወይም ባይመዘገብም እስከ የካቲት 30 ቀን 2013 ዓ.ም ድረስ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን ዕቃዎች ማምረት ወይም ወደአገር የማስገባት ወይም አገልግሎት የመስጠት ሥራ ማከናወን ይችላል፡፡"

//